*** ትምህርተ-ስላሴ ዘላለማዊው እውነት ***
በ'ወንጌላዊ' ሳሂህ
06/05/2013 ዓመተ ምህረት የተፃፈ
(ክፍል #2)

በክፍል አንድ ዝግጅቴ በዚህ ርዕስ ዙሪያ ጥቂት መንደርደሪያ ቢጤ ነገር ካልኩ በኻላ ሁላችሁም እንደምታስታውሱት 'ትምህርተ-ስላሴን አስመልክቶ ሊታወቁ የሚገባቸው ነጥቦች' በሚል ንዑስ ርዕስ ስር የመጀመሪያ ነጥብ የሆነውን 'ቃሉ ባይኖርም.....' የሚል ሀሳብ አንስቼ አንዳንድ ነገሮችን ብያለሁ። ይህ የክፍል ሁለት ዝግጅቴ ደግሞ ከዛው የቀጠለ መሆኑን እየገለፅኩ ወደ ንባቡ በቀጥታ እገባለሁ።

#ነጥብ_2፦ በስላሴ አካላውያን መካከል ከፍቅርና ከፈቃደኝነት የመነጨ መታዘዝ አለ፦

፡

በብዙ ሰዎች ዘንድ ያለ የአምላክ ምስል(ግንዛቤ) እጅግ የሚያስጨንቅ፤ ለማንም ገቢ የማይል፤ ሁሉን ማንበርከክ #ብቻ የሚያውቅ እና ገቢ ማለትንም እንደ ውርደት የሚቆጥር ከመሆኑ የተነሳ በስላሴ አካላዊያን ዘንድ ከፍቅርና ከትህትና የመነጨ የእርስ በእርስ መታዘዝ አለ ሲባል የሚደነግጡ እና የሚያላግጡ ብዙዎች ናቸው። ይህ ለእኛ የሚነግረን ደግሞ እነዚህ ሰዎች አምላካችን የሚሉት አካል ምን ያህል ትዕቢተኛ መሆኑን ነው።

፡

መፅሀፍ ቅዱስ ግን ሚስት ከባሏ በባህርይ(Nature or essence) ሳታንስ በፍቅርና በትህትና እንዲሁም በፈቃዷ እንድትታዘዘው እንደሚያስተምረው ሁሉ በስላሴ አካላዊያንም መካከል በፈቃደኝነትና በፍቅር ላይ የተመሠረተ የእርስ በእርስ መታዘዝ እንዳለ ያስተምረናል። ይህ ታዲያ በሌላ መልኩ በስላሴ አካላዊያን መካከል 'ማን ከማን ይበልጣል' የሚል የፉክክር መንፈስ አለመኖሩን የሚያስረዳ ነው። በዚህ ደግሞ ስላሴ የትህትና ሞዴላችን ነው ልንል ድፍረት አግኝተናል።

፡

እዚህ ጋር ገቢ ማለት ወይንም አንድን አካል መታዘዝ የባህርይን(Nature) ማነስ ያሳያል ለሚሉን ልብ-አውልቆች አንድ ጥያቄ ጠይቀናቸው ማለፍ ግድ ይለናል። ይኸውም መታዘዝ የባህርይ ማነስን ወይም መጉደልን የሚያሳይ ከሆነ እንግዲያውስ መፅሀፍ ቅዱስ ኢየሱስ ለአብ እንደታዘዘ ብቻ ሳይሆን የሚነግረን ለእናቱ ለቅድስት ብፅዕት ማርያምም መታዘዙንም ጭምር ነውና(እባክዎን፦የሉቃስ ወንጌል 2:51 ያንብቡ) በተመሣሣይ መልኩ ከእናቱ ከቅድስት ማርያምም በባህርይ(Nature)ያንሳል ማለት ይኖርብናል።

በተጨማሪም መፅሀፍ ቅዱስ ሴት ልጅ ለባሏ ልትታዘዝ እንደሚገባ እንዲሁም ልጆች ለወላጆቻቸው ሊታዘዙ እንደሚገባ ያስተምራልና በተመሣሣይ መልኩ ሴት ልጅ ከባሏ እንዲሁም ልጆችም ከወላጆቻቸው በባህርይ(Nature) ያንሳሉ ብለን ልንደመድም ግድ ይለናል።

፡

ነገር ግን ይህን ባላደረግንበት ሁኔታና አግባብ የኢየሱስን ለአብ መታዘዝ ብቻ ቦጭቀን 'ኢየሱስ ለአብ መታዘዙ ከአብ ያነሰ መሆኑን ያሳያል' ልንል አንችልም። ይህ ፍርደ-ገምድልነት ነውና።

#ነጥብ_3 መፅሀፍ ቅዱስ 'እግዚአብሔር' ሲል ምን ማለት ፈልጎ እንደሆነ መታወቅ አለበት።

'እግዚአብሔር' የሚለው ቃል 'እግዚ' እና 'ብሄር' ከሚሉ ሁለት የግዕዝ ቃላት የተመሠረተ እንደሆነ የሚታወቅ ነው። 'እግዚ' ማለት ጌታ ሲሆን 'ብሄር' ማለት ደግሞ ህዝብ ወይንም ዓለም የሚል ትርጉም እንዳለው የቋንቋ ሊቃውንት ያስረዳሉ።

፡

ይሁንና ግን ይህን እውነታ መቀበል የማይፈልጉ አንዳንዶች ይህን እውነት ላለመቀበል ሲሉ ያለምንም ሀፍረትና መሸማቀቅ 'እግዚአብሔር' በተባለበት ቦታ ሁሉ 'አብ'ን ለማመልከት ነው የሚል ጭፍን አቋም ይዘዋል። ታዲያ ይህን ሲሉ አንዳንዶች እንደሚመስላቸው 'እግዚአብሔር' የሚለውን ቃል ትርጉም ስላላወቁ አይደለም። ይልቅስ ሆነ ብለውና 'እግዚአብሔር' ለሚለው ቃልም ተገቢውን ትርጉም ቢቸሩት የሚቆሙለት አስተምህሮ እንደሚናድ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ነው።

፡

በእርግጥ በአንዳንድ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች 'እግዚአብሔር' የሚለው ቃል በግልፅ አብን ብቻ ወክሎ ቀርቧል። ይህን ማንም አልካደም። ነገር ግን ግጭቱ የሚነሳው 'እግዚአብሔር' በተባለበት ቦታ ሁሉ አብን ብቻ ነው የሚወክለው የተባለ ጊዜ ነው። እጅግ በብዙ

ቦታዎች 'እግዚአብሔር' የሚለው ቃል ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ወክሎ ቀርቧልና።

፥

ይህ የሚያሳየው ደግሞ 'እግዚአብሔር' የሚለው ቃል አብን ብቻ ሳይሆን ወልድንና መንፈስ ቅዱስንም ጭምር የሚወክል የወል ስም መሆኑን ነው። ስለሆነም ይህን እውነት ተቃርኖ 'እግዚአብሔር' የሚለው ቃል ሁልጊዜም ቢሆን አብን ብቻ ነው የሚወክለው ማለት - ነጭ ቅጥፈት ነው!

#ነጥብ_4 ትምህርተ-ሰላሴ ሚስጥር ነው ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል።

እንደሚታወቀው ትምህርተ-ሰላሴ በመፅሀፍ ቅዱሳችን እጅግ ከተብራሩና ከተተነተኑ ትምህርቶች መካከል አንዱ ነው። ከዚህም የተነሳ ደግሞ አንድ ሰው በቅን ልቦናና እውነት በሚፈልግ ልብ ሆኖ መፅሀፍ ቅዱስን ቢያነብ መጀመሪያ የሚረዳው ትምህርት ቢኖር ትምህርተ-ሰላሴን ነው።

፥

ይሁንና ግን ይህ ማለት ስለ ትምህርተ-ሰላሴ ሁሉም ነገር ተብራርቶአል ወይንም ተተንትኗል ማለት አይደለም። ይህም የሆነው ፈጣሪን ጠንቅቀን ሙሉ በሙሉ ማወቅ ስለማንችል እንጂ ትምህርቱ በራሱ ግልፅና ጥርት ያለ ስላልሆነ አይደለም። ለድነታችን ከበቂ በላይ የሆነ ትምህርት ተገልጦልናል።

፥

በሌላ መልኩ 'ትምህርተ-ሰላሴ ሚስጥር ነው!' ስንል እግዚአብሔር #እንደማናቸውም የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርቶች ልቦናችንን ካላበራው በቀር በራሳችን ጥረት ብቻ ልንገነዘበውም ሆነ ልንረዳው አንችልም ማለታችን ነው እንጂ(ይህንን መረዳታችንን የሚደግፉ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል 1 ኛቆሮ 2:14, 2 ኛቆሮ 4:3-4, 2 ኛተሰ 2:10)።የሰው ልጅ ፈፅሞ የሚረዳው ትምህርት አይደለም፤ ወይንም ደግሞ ትምህርቱ የማይፈቱ ብዙ ድብብቆሽን የያዘ ነው ማለታችን አይደለም።

፥

በመሆኑም ከዚህ ሐቅ በተቃራኒ 'ትምህርቱን ለምንድን ነው ሚስጥር ነው የምትሉት?' የሚሉን ሰዎች ባይገባቸውም እየነገሩን ያለው 'አምላካችን በአይምሮአችን ልክ የተሰፋ ነው!' የሚለውን ነው።

#ነጥብ_5 መፅሀፍ ቅዱስ 'እግዚአብሔር አንድ ነው' ሲል ምን ማለት ፈልጎ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል፦

መፅሀፍ ቅዱስ ከዘፍጥረት-ራዕይ ድረስ ስለ እግዚአብሔር አንድነት በሚናገርበት ጊዜ አካላዊ ሶስትነቱን ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንጂ በካደና በደፈጠጠ መልኩ አይደለም። ይሁንና ይህን በውል ያልተገነዘቡ ምስኪኖች በመፅሀፍ ('ጌታ አንድ ነው፤ ከእኔ በቀር ለሌሎች አማልክት የሚሰዋ ቢኖር ይገደል፤ ከእኔ በቀር አምላክ የለም፤ ከእኔ ውጪ ያለን አካል አታምልክ አትሰዋለትም፤....ወዘተ) የሚሉ ክፍሎችን የሚረዱበት መንገድ የተንሸዋረረ ሆኗል።

፥

እነዚህ ሰዎች ታዲያ ምንም እንኳን ማስረጃ ባይኖራቸውም(ባያቀርቡም) በእነዚህ ምንባባት ላይ ተናጋሪው አብ እንደሆነና ንፅፅሩንም እያደረገ ያለው ከወልድ እና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንደሆነ አድርገው ነው የሚያስቡት።

፥

ለዚህ ሁለት ማሣያዎችን ላቅርብ። የመጀመሪያው፦ 'ታላቅ ምክር
ለአዲሱ ትውልድ' በተሰኘው የቡመር አርሲ መፅሀፍ ገፅ 25 ላይ ያገኘሁት ፅሁፍ ነው። ፀሀፊው ኢሳ 44:8 ሲያብራራ እንዲህ ይላል፦"....ከእኔ ሌላ አምላክ አለን? አምባ የለም፤ ማንንም አላውቅም(ኢሳ 44:8)። 'ማንንም አላውቅም' ማለቱ ኢየሱስንና መንፈስ ቅዱስንም ጨምሮ በጌትነት አላውቃቸውም፤ ማለቱ ነው።" ይላል። ሁለተኛው ማሣያዬ ደግሞ ፓስተር ኤልያስ ሽባባው የተባለ 'የሐዋርያት ቤ/ክያን' ፀሀፊ 'የሰላሴ አጠያያቂ ምስጢር...' በተሰኘ መፅሀፉ ያለው ነው። እንዲህ ይነበባል፦ " ማር 12:32 ... አንድ ነው ከእርሱም በቀር ሌላ የለም፤ አንድ ነው ብሎ ሌላ የለም ሲልና እኔ ብሎ ከእኔ በቀር ሌላ የለም ማለቱ አንድ እግዚአብሔር ውስጥ ብዙ አባላት ወይም አካላት እንደሌሉ ያመለክታል። በተጨማሪም ብቻውን የሚለው ቃል በቡድን ህብረት እና አንድነት የሚባሉ ቃላትን ለእግዚአብሔር መጠቀም እነደማይገባ የሚያመለክት ነው።.....ስለዚህ ለትምህርተ-ሰላሴ አስፋፊዎች አላነቃንቅ ካሏቸው የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል 'ከእኔ ሌላ አምላክ ማንም የለም' እና 'ብቻዬን' የሚሉ ጥቅሶች በዋነኝነት ይጠቀሳሉ። በተለይ በተለይ እነዚህ ቃላት አምላክ ከሚለው ቃል ጋር ሲገቡ የስላሴ አባላት የሚባሉ አካላት እንደሌሉ ስለሚያረጋግጡ ፈተና ሆነውባቸዋል።

ትምህርታቸውንም ሙሉ በሙሉ ያፈርሰዋል።" ገፅ -33

የሰው ልጅ የፈለገውን ሀሳብና አመለካከት የመከተል ሙሉ መብት ስላለው ፖስተሩም ሆነ ዑስታዙ ይህን በማመናቸው ለምን እንዲህ አመናችሁ አይባሉም። ይሁን እንጂ ግን ደግሞ በዚህ ትምህርታቸው የዋሹት እውነትን በመሆኑና በዚህ ትምህርታቸውም አምኖ የሚጠፋው ሰው ብዙ ስለሆነ ተሳስታችሀኻል ወደ ቀልባችሁ ተመለሱ ሊባሉ ግድ ነው። ስለሆነም መፅሀፍ ቅዱስ እግ/ር አንድ ጎው ሲል ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ማግለሉ ለመሆኑ የሚዋጥ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። ይነተረካሉ። ይወተወታሉ።

፥

እኛ ግን 'ከተባፈው አትለፍ' በሚል የቃሉ መልህቅ ላይ ሆነን እውነቱን ስንናገር። 'እግዚአብሔር አንድ ነው' በሚለው ቃል እና 'አብ አንድ ነው' በሚለው ቃል መካከል ትልቅ ልዩነት አለ ብለን እንጀምራለን። እግ/ር ማለት አብ ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ማለት የዓለም/የህዝብ ጌታ ማለት እንጂ። እንዲሁም አብ ማለትም እግዚአብሄር ማለት አይደለም አባት ማለት እንጂ።

፥

ስለሆነም እግዚአብሔር በተባለበት ቦታ ሁሉ አብ ለሚታያቸው ወገኖቻችን ማስተላለፍ የምንፈልገው መልዕክት 'እግዚአብሔር አንድ ነው' በሚለው ንግርት ውስጥ ተናጋሪው አብ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሶልዲ ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ቃሉ እንዲቀኝላችሁ የምትፈልጉትን ቅኝት እንዲጫወትላችሁ አታስገድዱት የሚል ነው። ቃሉ 'እግዚአብሔር አንድ ነው' አለ እንጂ 'አብ አንድ ነው' አላለም(በነገራችን ላይ አብ አንድ ነው ቢል እንኳን ስለአብ አንድነት እየተናገረ ነው የሚባለው እንጂ ወልድና መንፈስቅዱስን እያገለለ ነው አይባልም)። እግዚአብሔር የሚለው ቃል ደግሞ ለሶስቱም አካላዊያን(አብ፣ ወልድና መንፈስቅዱስ) በእኩልነት የሚያገለግል የወል ስም ነው።

፥

ስለሆነም በሁሉም የመፅሀፍ ቅዱሳችን ክፍሎች እግዚአብሔር እኔ ብቻ አምላክ ነኝ፤ ከእኔ በቀር ለሌላ አካል የሚሠዋ ቢኖር ይሙት፤...ወዘተ የሚሉ ንግግሮችን ሲያደርግ ንዕዕሩ ሁልጊዜም ቢሆን ከጣዖታት ጋር እንጂ ከሌላ የስላሴ አካል ጋር አለመሆኑ ሊታወቅ የሚገባው ነው።

፥

ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን ይህን አንተ የምትለውን አንቀበልም የሚል ሰው ካለ። የፈለገውን ማመንና መቀበል መብቱ እንደሆነ እየነገርኩት ግን ደግሞ ለአቋሙ ፥አጥጋሚ ማስረጃ አንዲያቀርብም ማሣሠብ እወዳለሁ።

#ነጥብ_6 'አካል' ለሚለው ቃል ምን ትርጉም እንደምንሰጥ ሊታወቅ ይገባል፦

የቋንቋ እና የአመክንዮ ምሁራን አንድ ውይይት በተሳለጠ ሁኔታ ይጠናቀቅ ዘንድ በምንጠቀማቸው ቃላት ዙሪያ የጋራ መግባባት ሊኖረን ይገባል የሚል ጠንካራ አቋም አላቸው። ታዲያ ይህ እጅግ ወሳኝ ነጥብ በመሆኑ ለማንኛውም የውይይት አጀንዳ መዋል የሚገባው ነው።

፥

ስለሆነም በዚህ ቦታ ብዙዎች የማይረዱትን ግን ደግሞ ትምህርተ-ስላሴን ለመረዳት እጅግ ወሳኝ ስለሆነው ቃል ይኸውም 'አካል' የተባለውን ትርጉም ፈንከት አድርገን እንመለከታለን። በጣም በሚያስገርም መልኩ ይህ ቃል በብዙዎቻችን ዘንድ 'የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስ፣ እና የሚታይ የሚል ትርጉም ብቻ ነው ያለው። እውነት ነው ይህ አንደኛው ትርጉሙ ነው።

፥

ይሁንና ግን አንድ ቃል ከአንድ በላይ ትርጉሞችን ሊይዝ ይችላልና። ይህም ቃል ከዚህ ያለፈን ትርጉም ይዟል።በተለይ እኛ በትምህርተ-ስላሴ የምናምን ሰዎች ይህን ቃል የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስ እና የሚታይ በሚለው ትርጉሙ አልተጠቀምነውም። አንጠቀምበትምም።

፥

ከዚህ ይልቅ 'አካል' የሚለውን ቃል ለትምህርተ-ስላሴ የምንጠቀመው 'ስሜት፣ ዕውቀትና ፈቃድ ያለው' በሚለው ትርጓሜው ነው። በሌላ አነጋገር ይህ ቃል ራሱን ችሎ 'እኔ' ማለት ለሚችል የሚውል ነው ማለት ነው። መፅሀፍ ፈጣሪ በማንም እንዳልታየና እንደማይታይ አበክሮ ካስተማረ እንግዲያውስ 'አካል' የሚለውንም ቃል በመጀመሪያ ትርጉሙ (ማለትም የሚታይ፣ የሚጨበጥና የሚዳሰስ በሚለው) አገልግሎት ላይ ማዋል ትክክል አይሆንም።

፥

በመሆኑም ተቃዋሚዎቻችን ጠንቅቀው እንዲያውቁት የምንፈልገው አንድ ሐቅ ቢኖር ከጥንትም አካል ለሚለው ቃል የሚጨበጥ የሚዳሰስና የሚታይ የሚለውን ትርጉም እንዳልተጠቀምን ሁሉ ዘሬም ሆነ ወደፊትም ይህን ትርጉም የማንጠቀም መሆኑን ነው።

፡

ትምህርተ-ስላሴን ስናብራራ የምንጠቀመው ትርጉም ስሜት ፈቃድና ዕውቀት ያለው የሚለውን ብቻ ነው። ይህ ደግሞ የሚታይና የሚዳሰስ ሆኖ ነገር ግን ስሜትም ሆነ ዕውቀት እንዲሁም ፈቃድ የሌለውን ሁሉ አካል አይደለም ይላል ማለት ነው። ለምሳሌ በዚህ ትርጉም መሠረት ድንጋይ፣ እንጨት፣ ውሀ፣ እሳት....ወዘተ አካል የላቸውም።

፡

በአንግሩ በዚህ ትርጉም መሠረት መልዐክ እና ነፍስ ምንም እንኳን የማይታዩና የማይጨበጡ ቢሆኑም ግን ደግሞ አካል አላቸው።

፡

በተመሣሣይ ሁኔታ 'አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አካል አላቸው' ስንል ይታያሉ፣ ይዳሰሳሉ እንዲሁም ይጨበጣሉ ማለታችን አይደለም። ከዚህ ይልቅ ሶስቱም አካላዊያን የራሳቸው ስሜት ዕውቀትና ፈቃድ አላቸው ማለታችን ነው። ወይንም ደግሞ እያንዳንዱ የስላሴ አካል ራሱን ችሎ 'እኔ' ማለት ይችላል እያልን ነው። --በዚህም ደግሞ እንዲህ ብለው ያስተማሩንን ቀደምት የቤ/ክያን አበው ፈለግ እንከተላለን።

፡

ከእዚህ መለስ ታዲያ ይህ ያላችሁት አልተዋጠልንም የሚሉ ወገኖች አንድ ማድረግ የሚኖርባቸው ነገር ቢኖር 'አብ፣ ወልድና መንፈስቅዱስ' የየራሳቸው ፈቃድ፣ ዕውቀትና ስሜት የሌላቸው መሆኑን ማሣየት ብቻ ነው። ይህን ማድረግ ካልቻሉ ስለማንሰማቸው ማለት ነው።

#ነጥብ_7 'ሶስቱም አካላዊያን በፈቃዳቸው አንድ ናቸው!' ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል።

አብ፣ ወልድና መንፈስቅዱስ የየራሳቸው 'እኔነት' (ማለትም የየራሳቸው ስሜት፣ ፈቃድና ዕውቀት) አላቸው ብለን የምናምን ክርስቲያኖች ይህን በመሠከረ አፋችን መልሰን 'ሶስቱም አካላዊያን በፈቃዳቸው አንድ ናቸው።' ስንል ግር የሚላቸው ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም።

፡

ታዲያ እነዚሁ ሰዎች ደንገጥ ብለው 'እንዴ?! አሁን ሶስቱም አካላዊያን የየራሳቸው ፈቃድ አላቸው ስትሉ አልነበረም ወይ ታዲያ አሁን ምን ተገኝቶ ነው ይህን ካላችሁ በኻላ መልሳችሁ በፈቃዳቸው አንድ ናቸው የምትሉን?' ሲሉ ይደመጣሉ።

፡

እነዚህ ሁለት አዋጆች ምን ማለት እንደሆኑ በቅጡ ያልተረዳ ሰው በእርግጥም እነዚህ አባባሎች እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ ሊመስለው ይችላል። ይሁንና ግን የሁለቱን አዋጆች ትርጉም በትክክል ከተረዳን በመካከላቸው አንዳችም ተቃርኖ እንደሌለ መገንዘብ አያቅተንም።

፡

'ሶስቱም አካላዊያን የየራሳቸው ፈቃድ አላቸው።' ማለት እያንዳንዱ የስላሴ አካል ያለ ሌላ አካል ጣልቃ ገብነት ይወስናል ወይም ይመርጣል ማለት ሲሆን። 'ሶስቱም አካላዊያን አንድ ፈቃድ አላቸው።' ማለት ደግሞ አንዱ የስላሴ አካል የመረጠውን ወይንም የወሰነውን ሌላኛው የስላሴ አካል አይቃረነውም ወይም ይቀበለዋል ማለት ነው።

፡

እዚህ ጋር አንድ ልንጠነቀቀው የሚገባ አመለካከት አለ። ይኸውም አንዱ የስላሴ አካል የወሰነውን ወይም የመረጠውን ሌላኛው የስላሴ አካል አያፈርሰውም ወይም አይቃረነውም ሲባል ልክ በሰዎች መካከል እንደሚሆነው ዓይነት እንደው ህብረታቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ብቻ ያልተስማማቸውንም ሆነ የጎረበጣቸውን ሀሳብ ሁሉ በትዕግስት ይቀበሉታል ማለት አይደለም።

፡

ከዚህ ይልቅ ሁሉም የስላሴ አካላት የሚመርጡት ምርጫ ወይንም ውሳኔያቸው ሁሉጊዜም ቢሆን ቅዱስ፣ መልካምና ፍፁም ስለሆነ አንዱ የስላሴ አካል የሚመርጠው ምርጫ የሁሉም ምርጫ ነው ማለት ነው። በሌላ አነጋገር በአንዱ አካል ምርጫ ሁሉም ይስማማሉ ማለት ነው።

፡

ይህም የሆነው ሁሉም አካላት በነገር ሁሉ ንፁህና ፍፁም ቅዱስ በመሆናቸው ነው። ስለዚህም በሁለቱ አዋጆች መካከል ምንም አይነት ተቃርኖ የለም ማለታችን ትክክል ነው ማለት ነው።

#ነጥብ_8 መፅሀፍ ቅዱስ ሶስቱን አካላዊያን አንድ ላይ በሚጠቅሳቸው ጊዜ የባህርይን(Nature) ወይም የስልጣን መበላለጥን ታሳቢ ባደረገ መልኩ አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

አንዳንድ የዋሀን መፅሀፍ ቅዱስ ሶስቱን አካላዊያን በአንድ ላይ በሚጠቅሳቸው ቦታዎች ብዙ ጊዜ አብን በቅድሚያ ጠቅሶ ወልድንና መንፈስቅዱስን በሁለተኛና በሶስተኛ ደረጃ ስለሚጠቅስ 'ይህ በአጋጣሚ የተከሰተ ሳይሆን በአካላዊያኑ መካከል ያለውን የባህርይ(Nature) ወይም የስልጣን መበላለጥ ለማሳየት በዓላማ የተደረገ ነው።' የሚል አመለካከትን አዳብረዋል።
፡
ይሁንና ግን ይህ ምንም አይነት መሠረት የሌለው አመለካከት ነው። ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ፦
1ኛ). መፅሀፎ ቅዱስ ሶስቱን አካላዊያን በአንድ ላይ በሚጠቅሳቸው ቦታዎች ሁሉ አብን በቅድሚያ አለመጥራቱ ነው። ለምሳሌ በይሁዳ 20 እና 21 ላይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ #በመንፈስ_ቅዱስም እየጸለያችሁ፥ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን #የጌታችንን_የኢየሱስ_ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ #በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ።" በማለት መንፈስ ቅዱስን በመጀመሪያ ላይ ጠቅሶ ወልድንና አብን ደግሞ አከታትሎ ጠቅሷል። በ2ኛቆሮ 13:14 ደግሞ ይሄው ሐዋርያ "#የጌታ_የኢየሱስ_ክርስቶስ ጸጋ #የእግዚአብሔርም_ፍቅር #የመንፈስ_ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን። አሜን።" በማለት ወልድን በቅድሚያ ይጠቅሰውና አብንና መንፈስ ቅዱስን ደግሞ አከታትሎ ፅፏል። ስለሆነም መቀዳደም የባህርይን(Nature) መባላለጥ አያሳይም ማለት ነው።

2ኛ). ሶስቱም አካላዊያን በአንድ ላይ በተግፋባቸው በሁሉም ቦታዎች ላይ አብን በቅድሚያ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በሁለተኛና በሶስተኛ ደረጃ ቢፃፉ እንኳን ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ ' የስም አሰዳደራቸው የባህርይ(Nature) ወይንም የስልጣን መበላለጣቸውን ያሳያል ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርሰን አይችልም። ስለሆነም የቃላቱ የቦታ አቀማመጥ የባህርይን(Nature) መበላለጥ ያሳያል ብሎ ማለት ምክንያታዊነት አይደለም።

እንደምሣሌም፦ ዮሴፍ፣ ዳዊትና ዮናስ ወደትምህርት ቤት ሄዱ። በሚለው ምሣሌ ላይ ዮሴፍ ከዳዊትና ከዮናስ በፊት ተፅፏልና በሰውነት ይበልጣቸዋል ማለት ነፈዝነት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም።
#ነጥብ_9 '....አንድ ናቸው።' ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። ፀረ-ስላሴያዊያን ትምህርተ-ስላሴን የሚቃወሙበት ጠንካራ ማስረጃ ሲያጡ ከሚያስጨሏቸው አባራዎች መካከል "አንዱ አምላክ ምንም እንኳን በሶስት አካላት ቢገለጥም ሶስቱም አካላዊያን በባህርይና በስልጣን #አንድ_ናቸው።' ከሚለው የስላሴ አማኞች አዋጅ ላይ '....አንድ ናቸው።' የምትለውን ቃል ብቻ ገንጥለው በማውጣት

''ስላሴያውያን ምንም እንኳን የአንድ አምላክ አማኞች ነን ይበሉ እንጂ 'እነዚህ ሶስት አካላዊያን በባህርይና በስልጣን አንድ ናቸው።' በሚለው አዋጃቸው 'አንድ' ያሉበት አፋቸው ሳይደርቅ ተመልሰው በልባቸው የደበቁትን መድብለ አማልክታዊነት የሚገልጥ 'ናቸው' የሚልን ብዝሀነት ጠቋሚ ቃል ይጠቀማሉ። ይህም ለሚያስተውል ሁሉ የተሰወረን መግለጥ ልማዱ የሆነ ጌታ በልባቸው የደበቁትን ጣዖታት እየገለጠባቸው ለመሆኑ ምስክር ነው።" ይላሉ።

እዚህ ጋር ከሳሾቻችን ይህን ሙግት ሲያነሱ እኛ ምን እያልን እንደሆነ ስላልገባቸው ነው ባልልም። የዚህ ጥያቄ መሠረታዊ ችግር ግን #አንድ_ናቸው የሚለው ንግግራችን ምንን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን አለመለየቱ እንደሆነ የሚታወቅ ነው።

አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ሶስት አካላት ይሁኑ እንጂ በባህርይ አንድ ናቸው የሚለው የክርስቲያኖች አዋጅ ላይ 'አንድ' የሚለው ቃል የሚወክለው የአብን፣ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን የባህርይ አንድነት ሲሆን። ከእርሱ ቀጥሎ የተቀመጠው 'ናቸው' የሚለው ቃል ብዝሀነትን የሚያሳይ እንዲሆን የተፈለገበት ምክንያት በባህርይ አንድ የሆነው አምላክ ብዝሀነት እንዳለው ለማመልከት ነው። በሌላ አነጋገር 'ናቸው' የሚለው ቃል ብዝሀ አማልክትን ታሳቢ ያደረገ ስላልሆነ ክርስቲያኖች በጓዳቸው የደበቁት ምንም አይነት ጣዖት የለም ማለት ነው። ከዚህ ይልቅ 'ናቸው' የሚለው ቃል የሚያመለክተው ብዝሀ አካላትን ብቻ ነው ማለት ነው። ባይሆን ጣዖት አምልኮ ሰዎች የማያምኑበትንና የማይቀበሉትን በግድ ታምኑበታላችሁ ብሎ መከሰስ ነውና ከሳሾቻችን ሆይ ራሳችሁን ከጣዖት አምልኮ ጠብቁ ልንላቸው እንወዳለን።

ነጥብ 10፦ ትምህርተ-ስላሴ የተገለጠው በጊዜ ሂደት(progressively) ነው።

ስለ ትምህርተ-ስላሴ ማወቅ ከሚኖሩብን መሠረታዊ ነጥቦች አንዱ ትምህርቱ #ልክ እንደብዙዎቹ የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርቶች በአንድ ጊዜ አለመገለጡን ነው። ይህም ማለት ትምህርቱ በጊዜ ሂደት እየበራ፣ እየተገለጠ እና እየደመቀ መጣ ማለት ነው።

፥

በቀደሙት አባቶች ዘመን ስለ ትምህርቱ የነበረው ግንዛቤና በአሁን ሰዓት በእኛ ዘመን ስለ ትምህርቱ ያለው ግንዛቤ በእጅጉን ልዩነት አለው። የቀደሙት አባቶች(ለምሳሌ፦ ብሉይ ኪዳናውያኑ) ስለ ትምህርቱ ያላቸው ግንዛቤ ምናልባትም አንዱ አምላክ በብዙ አካላት መገለጡን ከማወቅ የዘለለ ላይሆን ይችላል። እኒህ አባቶች(ብሉይ ኪዳናውያኑ) በአንዱ አምላክ ያሉ አካላዊያን እነማን እንደሆኑ፤ የእርስ በእርስ ግንኙነታቸው ምን እንደሚመስል፤....ወዘተ ያሉ ጥያቄዎችን እኛ ከእነርሱ በኸላ የመጣን የትምህርቱ አማኞች እንደምናውቀው አያውቁም። ስለዚህም ትምህርቱን አስመልክቶ በቀደሙ አባቶችና በእኛ መካከል
የዕውቀት(የይዘት አላልኩም) ልዩነት አለ ማለት እንችላለን።

፥

ዕውቀት በባህርይዋ የምታድግና የምትሰፋ እንደመሆኗ ትምህርተ-ስላሴንም በተመለከተ ባለ እውቀት ላይ በትውልዶች መካከል ልዩነት አለ ማለት ከዚህ የዕውቀት መሠረታዊ መርሀ ጋር መስማማት ነው። በአንባሩ አንድ ትምህርት አውነት የሚባለው በትውልዶች መካከል ትምህርቱን አስመልክቶ ምንም አይነት የዕውቀት ልዩነት ከሌለ ነው ማለት ደግሞ ትልቅ ስህተት ነው።

፥

እዚህ ጋር 'ትምህርተ-ስላሴን አስመልክቶ በትውልዶች መካከል የዕውቀት ልዩነት አለ' ሲባል አንዳንዶች ልንል የፈለግነውን ነጥብ ጠምዝዘው ለራሳቸው ፍላጎት ሊጠቀሙበት ስለሚችል ይህ ንግግራችን ምን ማለት እንደሆነ እና ምን ማለት እንዳልሆነም አጥርተን መሄድ ይኖርብናል።

፥

ስለሆነም 'ትምህርተ-ስላሴን አስመልክቶ በትውልዶች መካከል የዕውቀት ልዩነት አለ' ስንል፤ እያልን ያለነው በእኛና በአባቶቻችን መካከል ትምህርቱን አስመልክቶ የይዘት ልዩነት አለ፣ እኛ የምናምነውና የምናውቀው ስላሴ አባቶቻችን ከሚያውቁትና ከሚያምኑት ስላሴ የተለየ ነው፣ ትምህርቱ በየጊዜው አዳዲስ መሻሻሎችን ያሳያል ወይንም ደግሞ እኛ ከአባቶቻችን በበለጠ ለመለኮታዊ ዕውቀቶችና ሚስጥሮች ብቁ ነን ማለት አይደለም።

፥

ከዚህ ይልቅ 'ትምህርተ-ስላሴን አስመልክቶ በትውልዶች መካከል የዕውቀት ልዩነት አለ' ስንል እያልን ያለነው ለትምህርቱ መጠሪያ የሚያገለግለውን ስም (ስላሴ የሚለውን) ከመስጠት ጀምሮ በተለያየ ዘመን በኖሩ ቅዱሳን አባቶች የታወቀውንና የታመነውን #ያንኑ ትምህርት በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ አስተማሩት ወይንም ደግሞ ትምህርቱ #ልክ_እንደ_ብዙዎቹ የመፅሀፍ ቅዱስ እውነቶች ከከዚህ ቀደሙ ዘመን በበለጠ አሁን በዚህ ዘመን ጥርት ብሎ ተገልጧል ማለት ነው።

፥

'የምንኖርባትን ምድር' በተመለከተ የቀድሞ ሰዎች ያላቸው የዕውቀት መጠን እና አኛ ሳይንስና ዕውቀት በተራቀቀበት ዘመን የምንኖር ሰዎች ያለን የዕውቀት መጠን የተለያየ ነው ማለት ምድር ቀድሞ ከነበረ ይዘቷ የተለየ ነገር ጨምራለች ወይንም እኛ የምናውቃት ምድርና የጥንት ሰዎች የሚያውቋት ምድር የተለያዩ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሁሉ። ስለ ትምህርተ-ስላሴ የቀድሞ አባቶች የሚያውቁት ነገርና እኛ ስለ ትምህርቱ የምናውቀው ነገር የተለያየ ነው ማለትም ትምህርቱ በየጊዜው ይዘቱን ይለዋውጣል ወይንም እኛ እና አባቶቻችን የምናምነው ስላሴ የተለያየ ነው ማለት አይደለም።
ትምህርቱ በዕውቀት ደረጃ እንጂ የይዘት ለውጥ አላመጣም ወይንም አላሣየም የሚለው እውነት ከሆነ ደግሞ በእኛና በአባቶቻችን መካከል መሠረታዊ የሆነና አንዳችንን ከድነት ሊያጎድል የሚችል ነገር የለም ማለት ነው። ምክንያቱም መሠረታዊው ዕውቀት አንድ አምላክ መኖሩን ማመንና ይህም አምላክ በሶስት አካላዊያን መገለጡን መቀበል ነውና፤ ይህን ደግሞ እኛም ሆንን አባቶቻችንን ያመንነውና የተቀበልነው እውነት ስለሆነ ማናችንም ከመዳን አንጎድልም ማለት ነው።

፥

በስተመጨረሻም ከዚሁ ነጥብ ሳንወጣ ልናስምርበት የሚገባው ሌላው ነገር ይህን 'ትምህርተ-ስላሴ የተገለጠው በሂደት ነው' የሚለውን ሀሳብ እንዲወክልላቸው የተለያዩ ክርስቲያን ፀሀፍት የተለያዩ አገላለጾችን(አባባፎችን) መጠቀማቸው ነው። ለምሳሌ አንዲሆነን ዊይን ግሩደምን እንውሰድ። ስልታዊ ነገረ-መለኮት በተሰኘ መፅሀፋቸው ገፅ 245 ላይ ይህንን ከላይ ያነሳነውን ሀሳብ እንዲህ በሚል አገላለፅ ገልጠውታል 'ትምህርተ-ስላሴ በብሉይ ኪዳን በግልፅ አልተገለፀም።'

፥

ረጋ ብሎ ከመርመር ይልቅ አስተያየት የሚቀናቸው አንዳንዶች ይህ የተባለበትን መንፈስ ካልተረዱ የብሉይ ኪዳን አባቶች ትምህርተ-ስላሴን እንደማያውቁ ስላሴያዊያንም ጭምር እየመሠከሩ ነው ሊሉ ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን ግሩደም ይህን ሲሉ ምን ማለት ፈልገው ነው ብሎ የሚመረምር አስተዋይ ሰው ግን ግሩደም ይህን ሲሉ ትምህርቱ በአዲስ ኪዳን በተገለጠውና በተብራራው መጠን አልተገለጠም ለማለት እንደፈለጉ ይገባዋል። ምክንያቱም እኒሁ ፀሀፊ ሩቅ ሳይሄዱ በዚሁ መፅሀፋቸው ላይ እንዲህም ብለዋልና '-ብዙ ምንባቦች (በብሉይ ኪዳን) እግዚአብሔር ከአንድ አካል በላይ ሆኖ እንደሚኖር ይጠቁማሉ። በአንድምታም ያመለክታሉ።'(ዝኒከማሁ)

፡

ስለሆነም ሌሎች ክርስቲያን ፀሀፍትም በተመሣሣይ መልኩ የትምህርተ-ስላሴን በሂደት መገለጥ(መታወቅ) በተለያየ አገላለጥ ሊያሳዩ ይችላሉና ፀሀፊዎቹ ምን ማለት ፈልገው እንደሆነ በውል ሳንረዳ ለአስተያየት አንቸኩል ማለት እወዳለሁ።

..... ይቀጥላል

@@@ መዝሙር @@@

<<ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ>>

ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ ሁሉን ቻይ ጌታ እግዚአብሔር!
ገና በማለዳ ወዳንተ ይቀርባል መዝሙር
ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ መሀሪና ሀያል!
ቡሩክ ስላሴ! እግዚአብሔር በሶስት አካል

ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ ቅዱሳን ሁሉ ያወድሱሀል
በመስተዋትማ ባህር ዙርያ የወርቅ አክሊላቸውን ያኖሩልሀል

ኪሩቤልና ሱራፌል በፊትህ ወድቀው
አንተ የነበርህ፤ ያለህና የምትኖረው።
ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ ጨለማ እንኳን ቢከልልህ
በሀጢያተኛ ሰው ሊታይ አይችልም ክብርህ

እነሆ አንተ ቅዱስ ነህ እንዳንተ ያለ ማንም የለም
በሀይልና በፍቅር በንፅህና አንተ ነህ ፍፁም
ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ ሁሉን ቻይ ጌታ እግዚአብሔር!
ሁሉም ስራዎችህ ስምህን ያወድሳሉ፤ በምድር በሰማይና በባህር

ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ መሀሪና ሀያል
ቡሩክ ስላሴ! እግዚአብሔር በሶስት አካል

(ዌይን ግሩደም 'ስልታዊ ነገረ-መለኮት' ገፅ #285, የመዝሙሩ ፀሀፊ፦ ሬጂናልድ ሄበር፣ 1826)
ዝማሬ መላዕክት ያሰማልን!